# ራስን ለመለወጥ ጥረት ቢደረግ

**ሲሳይ አለባቸው ከየካ**

ኢትዮጵያ ያላት ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ትኩረትን የሚስብ ነው፡፡ የአገሪቱ ጂኦ ፖለቲካዊ መልካም ምድራዊ አቀማመጥ ዋና ዋና የተባሉ የንግድ መሥመሮችን በመቆጣጠር እምቅ ሀብቷን ለመበዝበዝ ለተደጋጋሚ ወረራዎች አጋልጧታል፡፡

በዚህም አገሪቱ በየወቅቱ ይደረጉ የነበሩ የውጭ ኃይሎች ወረራን እንድታስተናግድ ተገድዳ ቆይታለች፡፡

በውስጥ ሥልጣንን ተቆጣጥሮ የጥቂቶችን አገዛዝ በሕዝቡ ላይ በመጫን በአገሪቱ ሀብት እንዳሻቸው ለመጠቀም በሚፈልጉ ኃይሎች በየጊዜው ሽኩቻዎች ይደረጉ ነበር፡፡

በዚህም ግቢያ ትናንት የታላላቅ ሥልጣኔዎች ቁንጮ ተደርጋ በዓለም ሕዝብ ዘንድ ትጠራ የነበረችው አገር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የረሃብ፣ የጦርነት፣ የድህነት፣ ተምሣሌት ተደርጋ ስትቆጠር ኖራለች፡፡

ከአገሪቱ የረዥም ጊዜ ታሪክ እንደምንረዳው የፖለቲካ ሥልጣን ራስን፣ ቤተሰብን፣ ጓደኛን ከፍ ሲልም የወጡበትን ጎሣ ወደ ሀብት፣ ብልፅግናና ክብር ሊያረማምድ የሚችል ብቸኛው መንገድ ነው።

ለዚህ ነው ‘ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል´ የሚለው አባባል በሕዝቡ ውስጥ ሰርፆ እንዲገባና እንደ ትክክለኛ ሥራ ሲቆጠር የነበረው።

ይህን ኋላ ቀር የኪራይ ሰብሳቢዎች አመለካከትና ተግባር ኢህአዴግ ደርግን በማስወገድ ከመሠረቱ የናደው ቢሆንም አሁንም ያለፈው ሥርዓት ርዝራዦችና አጫፋሪዎቻቸው አጋጣሚ ባገኙ ቁጥር ይህንኑ ለማራመድ ሲቋምጡ ይስተዋላሉ፡፡

ኢህአዴግና የሚመራው መንግሥት ገና ከጅምሩ ሥልጣንን በማጋራት የሽግግሩ ወቅት በሠላም እንዲጠናቀቅና በሕዝቡ ውስጥ መተማመን እንዲፈጠር አድርጓል።

ለዘመናት የሕዝቦች ጥያቄ የነበሩና ያለፉት ሥርዓቶች ሊመልሱ ያልደፈሩትን የሕዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን የማክበርና የማስከበር መብቶችን በህገ መንግሥቱ በዋናነት በመመለስ የኪራይ ሰብሳቢዎችን የዘመናት የሀብት ማፍሪያ ጥገት እንድትነጥፍ አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ህገ መንግሥቱ የብዙኃን ፓርቲ ሥርዓትን የሚፈቅድ በመሆኑ በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አገር አቀፍ ምርጫ ተካሂዶ የሕዝቡን አመኔታ ያገኘ ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣንን እንዲይዝ አድርጓል።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በነፃነት የራሳቸውን አካባቢ በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ማስተዳደርን፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ መጠቀምንና ማሳደግን ተግባራዊ አደረጉ።

ይህ ለዘመናት ሲናፍቁትና ሲታገሉለት የነበረው መብት በህገ መንግሥቱ በግልፅ ሲሰፍር ኪራይ ሰብሳቢዎች አርፈው አልተቀመጡም፤ ይልቁንም በተደራጀ ሁኔታ ሕዝቡን ወደማወናበድ ነበር የገቡት።

ራስን በራስ ማስተዳደር እስከመገንጠል መብት በሕዝቦች መካከል መለያየትን፣ መከፋፈልንና ልዩነትን በማስፋት ኢትዮጵያን ይበታትናታል በማለት ነበረ ዘመቻ የተከፈቱት፡፡

በእነሱ አመለካከት እና ከዚህ በፊት ያራምዱት በነበረው አቋም የኢትዮጵያ ጠባቂ ለነፃነቷና ለአንድነቷ ሟች ትምክህተኛው ኃይል ብቻ ነው፡፡

ሌላውን የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ግን የማስተዳደር ችሎታ፣ አገራዊ ራዕይና ፍቅር የሌለው ሁሌም ለመገንጠል የሚያልም አድርገው ሲስሉት ኖረዋል፡፡ በዚህም ሕዝቦች የፍትህ፣ የእኩልነና የመብት ጥያቄዎችን ሲያነሱ ጦር ሲያዘምቱባቸውና ሲያሳድዱዋቸው ቆይተዋል፡፡ እውነታው ግን ይህ አልነበረም።

ኢህአዴግና የሚመራው መንግሥት በህገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የብሔሮች እኩልነት እንዲረጋገጥና ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው እንዲወስኑ በአገሪቱ ውስጥ ባሉ ምክር ቤቶች እንዲሳተፉና እንዲወከሉ አድርጓል።

በመሆኑም ነፍጥ አንስተው ለነፃነታቸው ይታገሉ የነበሩ ድርጅቶች በተገኘው ሠላም ተጠቅመው ሕዝቡን ለልማት በማነሳሳት የአካባቢያቸውን፣ የክልላቸውንና የአገሪቱን ዕድገት በማፋጠን በኩል ትልቁን ሚና እንዲጫወቱ አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የማንነት፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ መልስ ካገኘ በኋላ አገራዊ አንድነታቸውን በተለያዩ ጊዜያት በማሳየት ኪራይ ሰብሳቢዎችን አሳፍረዋል፤ ይገነጣጠላሉ፣ ይበታተናሉ ተብለው በፀረ ሕዝቦች የቅድሚያ ግምት የተሰጣቸው ክልሎች በኢትዮ - ኤርተራ ጦርነት፣ በህዳሴው ግድብና ወ.ዘ.ተ ተሳትፏቸውን በማረጋገጥ የአንድነታቸውን ቃል ኪዳን በደም ቀለም ጽፈዋል።

ያለፉት 21 ዓመታት የሚያረጋግጡት የሕዝቦች ማንነት እስከተከበረ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በሠላማዊ መንገድ ችግሮቻቸውን እየፈቱ አንድ ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ ማኅበረሰብን ለመፍጠር በጋራ መሥራታቸውን ነው።

አገሪቱ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ልማት ለማረጋገጥ በሚያስችላት ትክክለኛ ራዕይና ተስማሚ ስትራቴጂ በመመራቷ ባለፉት ስምንት የተሳኩ የልማት ዓመታት በድርብ አኃዝ የሚለካ አጠቃላይ ዕድገት በማስመዝገብ በክፍለ አህጉሩ እና ከዚያም ባለፈ ደረጃ ልዩ ትኩረት የሚያሰጣት አፈፃፀም አስመዝግባለች ።

በዚህ ሰኬት የዜጎችን የልማት ተጠቃሚነት በማረጋገጥ አገሪቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው አገሮች ተርታ የሚያንደረድራትን ጎዳና ይዛለች።

ከዚህ አኳያ መንግሥት የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ከማሳካት ባለፈ እና በቀደመ ሁኔታ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነድፎ የምጣኔ ሀብት ዕድገቱ ቀጣይነት ይበልጥ ለማረጋገጥና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት እየሰራ ይገኛል፡፡

ይህን የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን እኩል ተጠቃሚነት የሚያረገግጠውን ምጣኔ ሀብታዊ ዕቅድ ሲተገብር ላለፉት ሁለት ዓመታት አበረታች ውጤት አስመዝግቧል።

ዕቅዱ ፈጣንና ቀጣይነት እንዲኖረው የሕዝቡ ተሳትፎ በተሟላ መልኩ መታከል ይኖርበታል፤ በመሆኑም ሕዝቡ የፖለቲካ ተሳትፎውን የሚያሳድግበትን ልዩ ልዩ መድረኮች በመፍጠር በአገሩ የዕድገት ጉዞ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን አድርጓል።

ኢህአዴግ የሚከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ መሥመር ልማታዊ በመሆኑ ከከፍተኛው አመራር እንስቶ እስከ ታችኛው የወረዳ አመራር ድረስ ያሉ ድርጅቱን በመወከል የመንግሥት ሥራን የሚተገብሩና የሚመሩ ታጋዮችን አመለካከትና ተግባር በየጊዜው እየፈተሸ የሚያስተካክልበት አሰራር አለው።

ይህ አሰራር ሕዝባዊ ወገንተኝነቱን በማጎልበት የኪራይ ሰብሳቢነትን ጎራ በማኮላሸት ድርጅቱ ሕዝቡ የጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ እንዲሄድ አስችሎታል።

ልማታዊ መንግሥት ማዕከል የሚያደርገው ብዙኃኑን ሕዝብ ነው፡፡ ይህን አካሄድ በመከተልና አጥብቆ በመያዝ ድርጅቱ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦችንና ስትራቴጂዎች በተግባር የሚተረጉሙ ለሕዝብ የወገኑ አመራሮቹን እውቅና እየሰጡ ለተጨማሪ ኃላፊነት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል የተሰለፉለትን ዓላማ በመካድ ሕዝባዊ ወገንተኝነታቸውን በግል ጥቅም የሚለውጡትን ኪራይ ሰብሳቢዎች በየትኛውም የሥልጣን እርከን ላይ ቢሆኑም በግልፅ በመገምገምና ለሕዝቡ በማጋለጥ እርቃናቸውን እንዲቀሩ ሕዝቡ ድርጅቱን ከኪራይ ሰብሳቢዎች ነጥሎ እንዲያይና እንዲታገላቸው በተለያዩ ጊዜያት የራሱን እርምጃ ወስዷል - ኢህአዴግ ሕዝባዊ ተቋም ነውና፡፡ የሚታገለውም የሕዝቦች ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ነው።

በዚህ በኩል ድርጅቱ በተለያዩ ወቅቶች ይህን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መሥመር ከትምክህተኞች ጎራ በመሰለፍ ለመበረዝ የመሥመር ልዩነት የሚያሳዩ አባሎቹንም ከተቻለ የመሥመሩን ኃያልነት እንዲቀበሉ ተጨማሪ ግንዛቤ በመፍጠር እንዲታደሱ ሲያደርግ የቆሙለትን ዓላማ ዘንግተው የድርጅቱን መለያ እምነቶች የሚሸረሽሩትን ከድርጅቱ በማባረር የመሥመሩን ኃያልነት አረጋግጧል።

የመንግሥት ሥልጣን ሕዝብን ለመጥቀም እንጂ የራስን የግል ፍላጎት ለማርካት እንዳልሆነ ኢህአዴግ በተለያዩ ግምገማዎች አባላቱን የማጥራት ሥራ ሕዝቡ በግልፅ የተገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በአመራርና በድርጅቱ ላይ እምነት እንዲያሳድር አድርጓል።

ኢህአዴግ ለዘመናት የአገሪቱ ችግር የነበረውን ሥልጣንን እንዴ ከያዙ የሙጥኝ የማለትን አካሄድ በቀየሰው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስትራቴጂ መሪዎቹን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ በመቀያየር ሊማሩ ለሚፈልጉ ኃይሎች ትምህርት ሰጥቷል።

ኢህአዴግ የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በማክበር ሁሉም ድርጅቶች ለወከላቸው ሕዝብ ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሰራር ዘርግቷል፡፡

በዚህም ግለሰቦች የመንግሥት ሥልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ መላውን የአገሪቱን ሕዝብ በእኩልነትና በታማኝነት እየመሩ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል፤ ኃላፊነታቸውን የዘነጉትን ከሥልጣን ያነሳል፤ ለሕዝቡ

ልማት ዕድገት፣ ለአገሪቱ ሠላም፣ ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች  እኩልነት የሚታገሉትን ይመርጣል፤ ለተሻለ ቦታ ያበቃል፡፡

ይህ አካሄድ በድርጅቱ ውስጥም ይተገበራል፡፡ ኢህአዴግ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ጉባዔዎች አመራሮቹን እየመረጠና እየተካ ለሠላማዊ የሥልጣን መተካካት መንገዱን ከፍቷል።

ይህ በብዙ አገሮች ሲተገበር የማይታየውና በኢህአዴግና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መሥመር ተከትለው በሚጓዙ አገሮች ብቻ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የመተካካት ሥርዓት ኪራይ ሰብሳቢዎች የሚያራምዱትን ሥልጣንን በቤተሰብ በጓደኛ በጎሣ የመያዝ አካሄድ እርቃኑን አስቀርቶታል።

ለዚህም ነው ኢህአዴግ ባለፉት ዓመታት የድርጅቱን መሪዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በምርጫ ሲቀይር ኅብረተሰቡ ውስጥ ውዥንብር ለመፍጠር ኪራይ ሰብሳቢዎቹ ላይ ታች ላይ ሲራሯጡ የሚስተዋሉት፡፡

ይህ በድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች የተወጠነውና ወደ ተግባር የተገባው ሠላማዊ የመተካካት ባህል ኅብረተሰቡ በድርጅቱ ላይ ያለውን አመኔታ የበለጠ አጠናክሮታል፡፡

ሕዝብና መንግሥት በጋራ በመሆን እየተገበሩት ያሉት የእድገትና የትራንስርሜሽን ዕቅድ የአገሪቱን ገጽታ በፍጥነት እየቀየረውና የሕዝቡን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ በመሆኑ ይበልጥ ፍጥነቱን ማሳደግ ይጠበቅበታል፡፡

ለዚህም አዳዲስ አመራሮችን ወደፊተኛው መስመር ማምጣት የግድ ይላል፡፡ የመጀመሪያው ዙር መተካካት ስኬታማ በሚያስብል ደረጃ ተግባራዊ የሆነውም ለዚሁ ነው።

መንግሥትና ሕዝቡ ለዚህ ተግባር ድጋፋቸውን ሲሰጡ የሥልጣን መተካካቱ ለአገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትና ለሠላማዊ የፖለቲካ ሽግግሩ አስተዋፅኦው የጎላ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

አለመታደል ሆኖ በኪራይ ሰብሳቢው ጎራ በአብዛኛው የተዋቀረው የተቃዋሚው ቡድን ዓለምን እያስደነቀ ያለውን የልማት ጉዟችንን በመደገፍ ይህን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት የበለጠ የሚያስቀጥል፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት የሚያጎለብት አጀንዳ በመያዝ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የሚደረገውን የሥልጣን መተካካት ወደ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ከፍ ያደርገዋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

ምክንያቱም አገራዊ አጀንዳ ካላቸው ውስን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውጭ ሌሎቹ የራሳቸው አጀንዳ የላቸውም፡፡

የአገሪቱን ጥቅም አሳልፈው ለመስጠት ወደ ኋላ የማይሉት እነዚህ ጥቂት ተቃዋሚ ተብዬዎች ሲያሻቸው ኢህአአዴግ የተወሰኑ ነባር ታጋዮች ድርጅት ብቻ ነው፤ በተደጋጋሚ እነዚህን ሰዎች ማየት ሰለቸን፤ ምነው ለአዲሶቹ ቦታ ቢለቁ በማለት ያላዝናሉ፡፡

ኢህአዴግ ባስቀመጠው የመተካካት ፖሊሲ እነዚህን ነባር ታጋዮች (አመራሮች) ለአዲሶቹ ቦታ ሲለቁና ልምዳቸውን ሲያካፍሉ አዛኝ በመምሰል ለፍተው…ለፍተው ተጣሉ፣ እነዚህ ግለሰቦች የወረዱት የዚህኛው ብሄረሰብ አባል ስለሆኑ ነው በማለት በብሄረሰቦች መካከል

ልዩነት ለመፍጠር ውዥንብር ይነዛሉ፡፡ ሲያሻቸው አዲሶቹ አመራሮች ልምድ የላቸውም፣ አገሪቱን ለመምራት አይችሉም፣ በመሆኑም ኢህአዴግ ሥልጣን ያስረክብ በማለት ይጮኃሉ። ዳሩ ምን ያደርጋል ! ሕዝብና መንግሥት ግን ጉዞአቸውን አላቆሙም።

በልማት ካደጉ አገሮች እንደምንረዳው ሠላም፣ ዴሞክራሲና ልማትን በአጠቃላይ ሕዝቡ እንደ ብቸኛ አማራጭ በመውሰድ ለስኬቱ እጅ ለእጅ ተያይዘው በመስራታቸው ነው፡፡

በዚህ  ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ግን ዕድገቱን ለማፋጠን በመንግሥትና በተቃዋሚ ወገኖች መካከል የሀሳብ ጦርነት ይኖራል።

ሕዝቡ የመንግሥትን አካሄድና የተቃዋሚዎችን ሀሳብ በመመርመር የራሱን ምርጫ ይወስዳል፡፡ ሂደቱ ግን በዚሁ ይቀጥላል።

ወደ አገራችን ተቃዋሚዎች ስንመለስ ግን በዋናነት የህዳሴውን ምሰሶ የሚቃወሙና ሂደቱን ለመናድ የሚሞክሩ፣ የተጀመረው ልማትና ዴሞክራሲ ወደ ኋላ እንዲራመድ ቀን ከሌት የሚጥሩ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ፡፡

የአገሬ ተቃዋሚዎች ራዕይ የላቸውም ብል ይቀለኛል፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያን እንደ አገራቸው በማየት እየተሰራ ያለውን ልማት፣ ሕዝቡ እያጣጣመ ያለውን ዴሞክራሲ ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ያቀዱት ዕቅድ የሚተገብሩት ስትራቴጂ የላቸውምና ነው፡፡

ለዚህም ነው አሁን ባሉት ተቃዋሚዎች አስተሳሰብ የሥልጣን ሽግግሩ ሊሳካና ሊካሄድ የማይችለው።

ኢህአዴግ ልማታዊ መንግሥት በመሆኑ ውግንናውም ከጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ነው፡፡ የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና ስትራቴጂዎች ሕዝቡን ከድህነት የሚያላቅቁ፣ አገሪቱ ራሷን ችላ ከተረጂነት እንድትላቀቅ የሚያደርግ ነው።

በዚህም ተሳክቶለት በተለያዩ ጊዜያት መላውን ሕዝብ ከጎኑ በማሰለፍ አገሪቱ ተከታታይነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት እንድታስመዘግብ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል።

ይህ የልማት ጉዞ የመላ ሕዝቡን ይሁንታ አግኝቶ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየተጓዘ ነው ሌላኛው የአመራር መተካካት ሂደት የተጀመረው።

ነፍሳቸውን ይማርና ታጋይ መለስ ዜናዊ በመታመማቸው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ሕዝብ ከመንግሥት የሚሰጡ መግለጫዎችን እያዳመጠ የተጀመረው ልማት ቀጣይነት እንዲኖረው የበኩሉን ጥረት ለማድረግ በሚዘጋጅበት ወቅት ቀድሞውኑ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ተቃዋሚዎች ከዳር ዳር ተጠራርተው ማላዘን ጀመሩ።

ከአቶ መለስ ህልፈት በኋላ አገሪቱ ትበታተናለች፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እርስ በርስ ይተላለቃሉ፣ ጦሩ ጎራ ለይቶ ይዋጋል፣ ካምፑን ለቆ ወደ ተመንደሩ ይገባል፣ ኢህአዴግ ውስጥ ከፍተኛ የሥልጣን ሽኩቻ ስለሚነሳ ድርጅቱ ይፈርሳል ወ.ዘ.ተ ከአገር ውስጥ እስከ ውጭ አገር ተቃዋሚ ተብዬዎች በመቀባበል አሚርተዋል፡፡

እዚህ ላይ ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባው ጉዳይ የአገሬ ተቃዋሚዎች የተጀመረው የሥልጣን መተካካት ወደ ሥልጣን ሽግግር ሂደት እንዳይጓዝ ራሳቸውን ከአገራዊ መድረክ አርቀው ከጠላቶቻችን ጎራ መሰለፋቸውን ነው።

መታወቅ ያለበት ቁም ነገር ቢኖር ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመንግሥት አስተዳደር ሥልጣኑን ቢይዙ የሚያስተዳድሩት አገሪቱን ነው፡፡ ታዲያ የተጀመሩ ከፍተኛ የልማት ሥራዎች፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች፣ የኢንዱስትሪ ግንባታዎች፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ጉዞ በሽግግሩ

ወቅት እንዳይደናቀፍ ሕዝቡን ማስተባበር ብሎም መንግሥትን ማገዝ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

አለመታደል ሆኖ ግን አፍራሽ እንጂ ልማታዊ ተቃዋሚ ለማግኘት አልቻልንም፡፡ በዚህ አኳኋን ደግሞ ዓለም በአድናቆት የሚመለከተውን ዕድገት አሳልፎ ለአፍራሾች መስጠቱን ሕዝቡ አይቀበለውም።

የአገሪቱን ዕድገት ቀጣይነት እንዲኖረው የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መስክ ባለፉት ስምንት ዓመታት
የተደረገው ጥረት ውጤት አፍርቷል።

ለዚህም ነው የታጋይ መለስ ሞት በተሰማ እለት ከዳር እስከ ዳር ሊባል በሚችል መልኩ ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው ያለቀሰው፡፡

የተጀመረውን የልማት፣ የዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብትና ሉዓላዊነትን የማስከበር እንቅስቃሴ ከዳር ለማድረስም ቃል የገባው።

በሌላ ጎኑ የሕዝብና የአገር ጠላቶች የሆኑ ኢህአዴግ ተከፋፈለ፣ ተሰነጣጠቀ የሚለውን ዜና ለማዳመጥ በቋመጡበት ወቅት ነው የሥልጣን መተካካቱ በሠላማዊ መልኩ የተጠናቀቀው።

ኢህአዴግ ቀደም ብሎ በአምስት ዓመት ውስጥ የመተካካቱን ሂደት እንጨርሳለን በማለት ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ አባላቱንና አመራሩን ከላይ እስከታች አወያይቶ የጋራ አቋም ይዟል፡፡

ይህ እውነት ያልመሰላቸው ተቃዋሚዎች ሠላማዊ የሥልጣን መተካካቱ ሲፈፀም ያሰቡትና ያለሙት ባለመሳካቱ ለሌላ ውዥንብር ራሳቸውን አዘጋጅተው ብቅ አሉ።

ኢህአዴግ ሕዝባዊ ነው፡፡ ኢህአዴግ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እንዲሁም ኃይማኖቶች ነው፡፡ ይህ ያልገባቸው ግን የዚህኛው ብሔረሰብ ውክልና በዛ፣ ያኛው ብሔረሰብ አልተወከለም የሚለውን ውዥንብር ቢያካሂዱም ሰሚ ጆሮ ሊያገኙ አልቻሉም።

ምክንያቱም መጀመሪያውኑ መንግሥት የሚመራው ብቃት ባላቸው ሰዎች እንጂ በብሄረሰብ ተዋፅኦ አይደለምና ነው፡፡

በመሆኑም ሕዝባችን የሚፈልገው የተጀመረው የሠላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ጉዞ እንዳይጨናገፍ እንጂ እንደ ኪራይ ሰብሳቢዎች የሥልጣን ጥያቄ አይደለምና እባካችሁን ራሳችሁን ለመለወጥ ሞክሩ ቸር እንሰንብት።